

# የሕዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ ጥሪ

**በዋሽንግተን ዲሲ ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን፣ ባቡሮችን (ሜትሮ) ፣ የሜትሮ አውቶብሶችን፣ የአገልግሎት ሰዓት፣ የስምሪት መስመሮችንና ክፍያ ላይ በታሰቡ ለውጦች እንዲሁም ለአቅደ ደካሞችና አካል ጉዳተኞች በሚሰጠው አገልግሎት (ሜትሮ አክሰስ) ፖሊሲ ሰነድ (Docket B10-2) ላይ በሚያደርገው ለውጥ የህዝብ አስተያየት መስማት ይፈልጋል!**

ዓላማ

የዋሽንግተን ዲሲ ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን ሊያደርጋቸው ባሰባቸው ለውጦች ላይ በሚከተሉት ቀናትና ቦታዎች ስድስት የህዝብ አስተያየት መስሚያ መድረኮችን (ሂሪንግ) አዘጋጅቷል።

**Hearing No. 548**
ሰኞ ማርች 22
Oakton High School Lecture Hall
2900 Sutton Road
Vienna, VA

**Hearing No. 549**
ረቡዕ, ማርች 24
St. Francis Xavier Church - Bailey Room
2800 Pennsylvania Avenue SE
Washington, DC

**Hearing No. 550**
ሰኞ, ማርች 29
Mt. Calvary Baptist Church
5120 Whitfield Chapel Road
Lanham, MD
TheBus will provide shuttle service to this hearing. Details at www.wmata.com

**Hearing No. 551**
ረቡዕ, March 31
Arlington County Board Room, 3rd Floor
2100 Clarendon Blvd.
Arlington, VA

**Hearing No. 552**
ሐሙስ, ኤፕሪል 1
All Souls Unitarian Church
Pierce Hall
1500 Harvard St. NW
Washington, DC

**Hearing No. 553**
ሐሙስ ኤፕሪል ፣ 1
Montgomery County Exec. Office Building
Cafeteria
101 Monroe St. (entrance on Jefferson St.)
Rockville, MD

**ሁሉም የአስተያየት መስሚያ መድረኮች (ሂሪንግ) የሚጀምሩት በ7 p.m. ሲሆን ከእያንዳንዳቸው በፊት ቀደም ብሎ 6:30 p.m ላይ የሚጀምር ለህዝብ ክፍት የሆነ ክፍለጊዜ አለ**

**በሁሉም መድረኮች ዊልቼር መጠቀም ይቻላል። ልዩ እርዳታ ወይም አስተርጓሚ የሚፈልጉ ዴኒስ ፔና በ202- 962 -2511 ወይም መስማት ለተሳናቸው በ202 638 3780 ፈጥነው መደወል ይችላሉ።**

metro

## ሪቂቅ ሀሳብ

ከጁላይ 1/ 2010 ጀምሮ ባለው የ2011 ዓመታዊ በጀት ላይ የዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን የ182 ቢሊዮን ዶላር የበጀት ጉድለት ይገጥመዋል። የሜትሮ አውቶብሶች፣ የሜትሮ ባቡሮችና ለአቅመደካሞችና አካል ጉዳተኞች የሚሰጡ የሜትሮ ትራንስፖርት አገልግሎቶች (ሜትሮ አክሰስ) በሙሉ ፈንድ የሚደረጉት በከፊል ከመንገደኞች ከሚገኘው ገቢ ሲሆን በከፊል ደግሞ ከዋሽንግተን ዲሲና ከሜሪላንድ መንግሥት፣ እንዲሁም ከተወሰኑ የቨርጂኒያ ግዛቶች ነው።

በመሆኑም የ2011 ዓመታዊ በጀት እጥረትን ለመቋቋም ሜትሮ ከመንገደኞች የሚያገኘውን ገቢ መጨመር፣ የአውቶብስ ስምሪት መስመሮችን በማሳጠር፣ የሜትሮንም ሆነ የአውቶብስ ስምሪት ሰዓቶችን በመቀነስና የሜትሮ አጠቃቀም ፖሊሲዎች ላይ ለውጥ ማድረግ ይኖርበታል።

ሊደረጉ በታሰቡ የመንገደኞች መሳፈሪያ የዋጋ ጭማሪ፣ የሰዓትም ሆነ የአገልግሎት ለውጥ እንዲሁም በአውቶብስ መስመሮች ለውጥ በ www.wmata.com ዌብሳይት ላይ ይፋ በሚደረገው ሰነድ ላይ የህዝብ አስተያየት ይፈለጋል። በስምሪት መስመሮችና በዋጋ ጭማሪው ላይ የሚደረገው ለውጥ ተግባራዊ እንዲሆን የታሰበው ከጁን 27 ቀን 2010 ጀምሮ ነው።

በተለይም ሜትሮ የበጀት ጉድለቱን ለማስተካከል በዋናነት ሊያተኩርባቸው ከፈለጋቸው ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል

1. የሜትሮ ባቡርና የአውቶብሶችን የመሳፈሪያ መነሻ ዋጋ እስከ $0.35. መጨመር

2. ከ3-6 ማይል ርቀት ያለውን የሜትሮ ባቡርና የአውቶብሶችን የመሳፈሪያ ዋጋ እስከ $0.055. ከዚያ 6 ማይል በላይ የሆኑትን ደግሞ እስከ $0.049 መጨመር

3. ሜትሮ ባቡሮችና አውቶብሶች እጅግ በጣም ቢዚ በሚሆኑባቸው ሰዓታት እስከ $0.50 የሚደርስ ሱር ታክስ እንዲከፈል ማድረግ

4. ሜትሮ ቢዚ ባልሆነባቸው ሰዓታት ባሉት አነስተኛው መደበኛ ዋጋዎች ላይ ለባቡሮች በ$0.30 ለአውቶብሶች ደግሞ $0.35 መጨመር

5. የመሣፈሪያው ዋጋው ረከስ ባለበት ሰዓት (ራሽ አወር ባልሆነ ጊዜ) ለአጭር ርቀት ለተከለሉት (first tier) መስመሮች ዋጋ ላይ እስከ $0.40 ለረጅም ርቀት( second tier) ደግሞ እስከ $0.50 ጭማሪ ማድረግ

6. የሜትሮ ባቡሮችና የአውቶብሶች መሣፈሪያ ዋጋ በቋሚነት እየጨመረ ይሄዳል። የመሣፈሪያ ዋጋና ሌሎች ክፍያዎች በፌደራል መንግሥቱ ደንብና የኮንትራት ስምምነት በሚያዘው መሠረት ሊፈጸሙ ይችላሉ።

7a. ከባቡር ወደ አውቶብስ፣ ከአውቶብስ ወደ ባቡርና ከአውቶብስ ወደ አውቶብስ የሚደረገውን የሽግግር (ትራንስፈር) ጊዜ ከ3ሰዓት ወደ 2 ሰዓት ዝቅ ማድረግ

7b. ከአውቶብስ ወደ ሜትሮ ከሜትሮ ወደባቡር የሚደረገውን መሸጋገሪያ ዋጋ ከነጻ ወደ $0.75 ሳንቲም ማስተካከል

7c. በእረፍት ቀናት በነጻ የሚደረገውን የአውቶብስ ሜትሮና የሜትሮ አውቶብስ አጠቃቀምዳግም መመርመር

8. መደበኛውን የሜትሮ መሳፈሪያ ዋጋ እስከ $4.00 ማድረግ ወይንም በእረፍት ቀናት ከሌሊቱ 12:01 AM ጀምሮ እስከ መዝጊያው ድረስ ያለውን በመደበኛ ዋጋ ማስከፈል

9. ቅናሽ የማይደረግባቸው የኤክስፐረስ አውቶብሶች መሳፈሪያ ዋጋን በ$0.90 ሳንቲም ፤ ለአረጋውያንና ለጦር አካል ጉዳተኞች ደግሞ እስከ $1.40 የሚደርስ ጭማሪ ማድረግ

10. ወደ ዳላስ ና ቦልቲሞር ኤርፖርት በሚሄዱት ሻትሎች መሳፈሪያ ዋጋ ላይ እስከ $2.90 መጨመር

11a. በካሽና በስማርት ካርድ አጠቃቀም መካከል ያለውን ልዩነት በ$0.50 ከፍ ማድረግ

11b. ከሜትሮ አውቶብሶች ላይ በስማርት ትሪፕ የሚገኘውን የ$0.10 ቅናሽ ማስቀረት

12. ለህጻናት ይፈቀድ የነበረውን ነጻ የሜትሮ ባቡርና የአውቶብሶችን የመሳፈሪያ እድሜ ገደብ ወደ 3 ዓመት ዝቅ ማድረግ

13. መደበኛ ባልሆኑ ልዩ መስመሮች ለአካል ጉዳተኞችና የቡድን ተጓዦች (የሜትሮ አክሰስ) የሚደረገውን ዋጋ ከመደበኛው ዋጋና መስመር ጋር አነጻጽሮ እስከ እጥፍ ማሳደግ

14. ከሜትሮ አክሰስ ጋር ተያይዞ የሚከፈለውን ክፍያ መጨመር በዞን 1 እስከ $4.00 በዞን ሁለት እስከ $8.00 for እንዲሁም ለዞን 3 እስከ $12.00 ለዞን 4 እስከ $16.00 ማድረግ

15. ሁሉንም የሜትሮ ፓርኪንግ ዋጋ መጨመር። በቀን የሚከፈለውን እስከ $1.15 ወርኃዊውን ክፍያ ደግሞ እስከ $13.75 መጨመር እንዲሁም የነጻ ፓርኪንግ ሰዓትን መቀነስ

16. በኮንትራንት የሚያዙ የፓርኪንግ ሰዓቶችን (Reserved Parking) ከ10 a.m. ወደ 9 a.m. መቀነስ

17. ዓመታዊ የብስክሊት መቆለፊያ ኪራይ ዋጋን (bicycle locker rental fee) እስከ $130.00. መጨመር

18. የሱር ታክስ የሚከፍልባቸውን ባቡር ጣቢያዎች ለማሻሻል እስከ ሁለት ከሚደርሱ ከዲሲ ቨርጂኒያንና ሜሪለንድ መውጪያና መግቢያ ባቡር ጣቢያዎች እስከ $0.05 የሚደርስ ሱር ታክስ ማስከፈል

19. ሁሉንም የሜትሮና የአውቶብስ ነጻ መተላለፊያ ቲኬቶችን መስጠት ማቋረጥ

20. በማናቸውም ሰዓት ለፓርኪንግ ማስከፈል

21. የበዓላትና የእረፍት ቀናትን የሜትሮ አገልግሎት ሰዓት መጨመር

22. በመደበኛ የሜትሮ ሰዓት የተወሰኑ የሜትሮ ጣቢያ መግቢያ በሮችና ከሜትሮው ውጭ የሆኑ የተያያዙ መተላለፊያና መሿለኪያዎችን መዝጋት

23. በእረፍት ቀናት ሞርገን ቡልቨርድን፣ ቼቨርሊ እና ዲንውድ ሜትሮ ጣቢያዎችን መዝጋት

24. የሜትሮ ባቡር ጣቢያዎች ክፍት የሚሆኑበት ሰዓት በሥራ ቀን 30 ደቂቃ በእረፍት ቀናት ደግሞ ለ1 ሰዓት እንዲራዘሙ ማድረግ

25. ዓርብና ቅዳሜ ምሽቶች ላይ በተቻለ መጠን የባቡር ጣቢያዎች ልክ እኩለ ሌሊት ሲሆን እንዲዘጉ ማድረግ

26. ከሐኒግተን እስከ ኪንግ ስትሪት ያለውን የየሎ ላይን (ቢጫ) ባቡር አገልግሎት የእረፍት ቀናትና የሌሊት ሰምሪትን ሰዓት መቀነስ

27. የአውቶብስ መስመሮችን እንደሚከተሉት ማስተካከል
    - እስከ 35 የሚደርሱ ረጃጅምና አጫጭር የስምሪት መስመሮችን ማቋረጥ
    - 65 በሚሆኑ ሌሎች ልዩና የተወሰኑት አጫጭር መስመሮችን ማቋረጥና አቅጣጫዎች መቀየር

28. በማርቲን ሉተር ኪንግ ዴይ፣ በፕሬዚዳንት ዴይ በኮሎምቦስ ዴይ እና፣ በቬትረንስ ዴይ ባቡሮችንና የሜትሮ አውቶብሶችን አገልግሎት መቀነስ

29. አውቶብሶችና ሜትሮ ባቡሮች በቋሚነት የሚሰማሩባቸውን አካባቢዎች ቀንና ቦታ ሰዓት በትክክል በመለየትና በማስታወቅ ለአካል ጉዳተኞችና ልዩ ተጓዦች የሚደረጉትን ልዩ ስምሪቶችን (MetroAccess service) መቀነስ

30. የሜትሮን ልዩ አገልግሎት እንደየሁኔታው የነጻ አገልግሎት ለሚፈቀድላቸውና የአካል ጉደተኝነት ማረጋገጫ ላላቸው ሰዎች ብቻ እንዲጠቀሙ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ

31. ከመደበኛው ዋጋ ውጭ የሆኑ ልዩ የመሣፈሪያ ቀናሾችን ወይም ፓሶችን ከ5 ጊዜ በላይ አለመስጠት፣ እንዲሁም እንደ ፕሬዚደንሺያል ኢናጉሬሽን፣ ወይም ታሪካዊ የፖለቲካ በዓላት ፣በትላልቅ የስፖርትና የመዝናኛ ዝግጅቶች ወቅት ለፓርኪንግ እስከ $25 ማስከፈል።

አዲሱ ፕሮጀክት ወይም የተሻሻለው የዋጋ ለውጥ ተግባራዊ የሚሆነው ከጁን 27 ጀምሮ ነው። በዚህ ፅሑፍ ያልተጠቀሱትን ጨምሮ፣ የበጀት ጉድለቱን አስመልክቶ ስለቀረቡ የመፍትሔ ሀሳቦች ሙሉ ዝርዝር በwww.wmata.com በሚለው ድህረ ገጽ መመልከት ይቻላል።

ፖሊሲው (በSection 62 of the WMATA Compact) በሚያዘው መሠረት ሜትሮ ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን 6 የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ መድረኮችን (ሂሪንግ) ያዘጋጃል። ስለ አስተያየት አሰጣጡና መድረኮቹ (ሂሪንግ) ያሉት መረጃዎች በየአካባቢው ቤተመጻህፍት (ላይብረሪዎች) በሜትሮ አውቶብሶችና ባቡሮች እንዲሁም በwww.wmata.com ይፋ ይደረጋሉ።

M

## በመድረኩ (ሂሪንግ) ቀርቦ  ለመናገር መመዝገብ የሚቻለው እንዴት ነው?

በቀረበው ሰነድ ላይ አስተያየታቸው እንዲደመጥ የሚፈልጉ ተጨማሪ ሀሳብም ሆነ ሌሎች አማራጮችን ለማቅረብ ለሚሹ ድርጅቶች ሆነ ግለሰቦች በሙሉ እድሉ ይሰጣቸዋል። አስያየታቸውን መስጠት የሚፈልጉ ዜጎችም ሆነ የድርጅት ተወካዮችም ከሆኑ የድርጅቱን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥርና ቀርበው መናገር የሚፈልጉበት ቀንና ቦታ ለይተው በ600 Fifth Street, NW, Washington, D.C. 20001. ለሚገኘው የዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን ጽ/ቤት ማሳወቅ አለባቸው። public-hearing-testimony@wmata.com ኢሜይል በማድረግ ወይንም በ202-962-1133 ፋክስ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በእያንዳንዱ ደብዳቤ ላይ የአስተያየት መስሚያ መድረኩን ማመሳከሪያ (ሂሪንግ ሪፈረንስ) ቁጥርና የአንደኛውን ተናገሪ ስም ብቻ መመዝገብ ይበቃል። የተናጋሪዎችን ስም ዘርዝሮ መጻፍ ተቀባይነት አይኖረውም። ለመናገር የተመዘገቡት ከተናገሩ በኋላ ምናልባት ሌሎች ሊናግሩ የሚችሉበት እድል ሊኖር ይችላል። የመንግሥት ባለሥልጣናት በቅድሚያ ለ5ደቂቃ ያክል ብቻ ከተናገሩ በኋላ ሌሎች አስተያየት ሰጪዎች እያንዳንዳቸው ለሁለት ደቂቃ ያክል ይናገራሉ። በተናጋሪዎች መካከል ደቂቃ መዋዋስም ሆነ ማስተላለፍ አይፈቀድም።

## በጽሑፍ የሚቀርቡ አስተያየቶችን እንዴት ማቅረብ ይቻላል?

በጽሑፍም ሆነ በአስረጅነት የሚቀርቡ አስተያየቶች እስከ ማክሰኞ ኤፕሪል 6/2001 ከሰዓት በኋላ 5 p.m ድረስ ብቻ በ 600 Fifth Street, NW, Washington, D.C. 20001. ለሚገኘው የዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን ጽ/ቤት መድረስ አለባቸው። ወይም በኢሜይል አድራሻ public-hearing-testimony@wmata.com  መላክ ይቻላል። በደብዳቤዎቹ ላይ የፖሊሲ ሰነድን ወይም የሂሪንግ ሪፈርንስ ቁጥሩን ማካተት ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ የህዝብ አስተያየት ድምጽ በሚቆጠርበት በwww.wmata.com/public_hearing_form. ዌብሳይት ድምፅም ሆነ ተጨማሪ አስተያየት መስጠት ይቻላል። የዌብ ሳይቱ አስተያየት በአካል ቀርቦ (በሂሪንግ) ከሚሰጠው በተጨማሪ ሲሆን ዌብ ሳይቱ ላይ የተጠቀሰው አድራሻም ሆነ ኢንፍሮሜሽን ለማንም አይገለጽም። ዌብ ሳይቱ ከዓርብ ማርች 19 ድረስ 5 ሰዓት 5 p.m. ጀምሮ እስከ ኤፕሪል 6/2010 ድረስ ለህዝብ ክፍት ሆኖ ይቆያል።